# የበላይነትን ለመተው አዋጅና ጸሎት

*አባት ሆይ ድንቅ አድርገህ ስለፈጠርከኝ አመሰግንሀለሁ። ምክንያቱ ደግሞ የፈጠርከኝ አንተ ስለሆንክ ነው። ስለወደድከኝና የአንተ ስላደረግከኝ አመሰግንሀለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስን የምከተልበትን እድል ስለሰጠኸኝ አመሰግንሀለሁ።*

*የበላይ የመሆንን ፍላጎት በማስተናገዴ ምህረትን አድርግልኝ። ከሌሎች የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ፍላጎቴ በመገዛቴም ይቅር በለኝ፤ እንደ ማንኛውም ሰው ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ። ያለ አንተም አንዳች ማድረግ አልችልም።*

*የኋላ ታሪኬን በምመለከትበት ጊዜም ሆነ አሁን ባለሁበት ሁኔታ በቡድን ውስጥም ባለኝ ግንኙነት የበላይ ለመሆን ለነበረኝ ፍላጎት ይቅር በለኝ፤ እኔም እክደዋለሁ። ሁሉም ሰዎች በአንተ ፊት እኩል መሆናቸውን አምናለሁ።*

*ሌሎችን ዝቅ የሚያደርግ ንግግርን በመናገሬ ይቅርታ አድርግልኝ። ለነዚህ ቃላቶቼ ምህረትን እጠይቃለሁ።*

*በዘራቸው፣ በፆታቸው፣ በሀብታቸውና በትምህርታቸው ምክንያት ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየትን እቃወማለሁ።*

*በፊትህ መገኘት የቻልኩት በጸጋህ ብቻ መሆኑን አውቃለሁ። በሰው ልጆች ላይ ሊደረግ ካለሁ ከማንኛውም ፍርድ እራሴን እለያለሁ። ያዳንከኝን አንተን ብቻ እመለከታለሁ።*

*ጻድቆች የበላይ ናቸው የሚለውን የሙስሊሞች አስተምህሮ እክዳለሁ። ሙስሊም መሆን ስኬታማ ያደርጋል፣ ሙስሎሞች የበላይ ሕዝቦች ናቸው የሚለውን እክዳለሁ።*

*ወንዶች ከሴቶች የበላይ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ አልቀበልም። ደግሞም እክዳለሁ።*

*የሰማዩ አባት እግዚአብሔር ሆይ ከነበረኝ ማንኛውም የበላይ የመሆን አስተሳሰብ እመለሳለሁ። አንተንም ለማገልገል መርጫለሁ።*

*ጌታ ሆይ በሌሎች ስኬት ለመደሰት መርጫለሁ። በሌሎች ላይ መቅናትና ጥላቻን አልቀበልም ደግሞም እክደዋለሁ።*

*ጌታ ሆይ በፊትህ ምን ዓይነት ሰው ስለመሆኔ ጤናማና ትክክለኛውን ፍርድ ስጠኝ፤ እንዴት እንደምታየኝ እውነቱን አስተምህረኝ። አንተ የምትፈልገው ዓይነት ሰው እንድሆንልህ እርዳኝ።*

*አሜን።*